# ጉልቻ ቢለዋወጥ...

“ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ” ይባላል በሀገርኛ። ከሰሞኑ የዘረኛው ወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ከስልጣኑ ለመልቀቅ መወሰኑን የዜና ማሰራጫዎች ሁሉ ሲያናፍሱት ሰንብተዋል። ይህንንም ወሬ ተከትሎ በአንዳንድ ገር ወይም የዋህ በሆኑ ኢትየጵያውያኖች ጎራ በሰፊው ሲየከራክርና ሲያወዛግብ ሰንብቷል፡ ፡ ጭራሹንም የሱ መልቀቅ እንደ ትልቅ ድልም ሆኖ እየተነገረ ነው።

በሌላም ጎን በታማኝ ተቃዋሚ ተብዬዎች ዙሪያ፣ ማለትም በእነልደቱ(ከሀደቱ) አንደበት የሱ መልቀቅ መልካም አለመሆኑ ሲሰበክልን ሰንብቷል።

እነኚህን ነገሮች አየሁና እኔም እንደ አቅሚቲ አንድ ልል እጄን ከብእር አገናኘሁ፡፡ መቼም ስለ መለስና የወያኔ ባህሪ ወይም ችግሩ ማውራት ጉንጭን ማድከም ይሆናል። ምክንያቱም አስራ ዘጠኝ አመት ሙሉ ተብሎ አልቋልና። ለምን ለመፍትሄ ፍለጋ እንቅስቃሴ እንዳልጀመርን አይገባኝም እንጂ ከልጅ እስከ አዋቂ ፣ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ፣ ከሰማይ እስከ ምድር ወያኔና ችግሩን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተገንዝቧል።

ይህ ዘረኛ መንግስት በጎሳ በማበጣበጥ፣ በሀይማኖት በማጋጨት፣ መሬትን ቁርሶ በመሸጥ እና የመሳሰሉትን ችግሮች በማስፋፋት ስልጣንን የሙጥኝ ብሎ ኖሯል እየኖረም ነው።

ነገር ግን ድንገት መለስ ስልጣን ላይ ለመቆየት ፍላጎት እንደሌለው ጭራሹኑም በፈቃድ የለቀቀ ቀዳማዊ የኢትዮጵያ መሪ መባል እንደሚፈልግም ደስኩሯል። እናም ወቱ እንዳለ ሆኖ በአንክሮ ሊታይ የሚገባው ጉዳይ ደግሞ አለ። ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም ነውና ነገሩ። የህዝብን መሪ ያውም እንስትን እስር ቤት ውሰቶ ጥሎ፡ ስልጣንን በፈቃደኝነት ለመልቀቅ መወሰንን መወሸከት እንደተለመደው የሁለት ምላስ ባለቤትነትን የሚረጋግጥ ሀቅ ነው።

እፍረት የለሹ መለስ የሀያ ሶስት አመት ተብዬዋን ልጁን በዚህ በኢንፎርሜሽን ዘመን መሳሪያ ተሸክማ አነጣጥራ ሰላማዊ ሰውን መምታት እንደምትችል ለዚህ አዲስ ትውልድና ታሪካዊ ህዝብ ፎቶዋንና የደከመ ዝናዋን ማቅረብ ፣ እኔ አባትየው ስልጣን ብተውም ተተኪው የትግራይ ተወላጆች አሁንም ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ህዝብ በጠመንጃ አፈሙዝ ከመግዛት ወደ ሁዋላ አይሉም የሚል ደማቅ መልእክትን የሚያንጸናባርቅ ታላቅ እውነታ ነው፡፡

በቅርቡ የዚሁ ዘረኛ ቡድን አባል ስበሃት ነጋ (ሲበላ ነጋ) እንደተናገረው በሀገሪቱ ላይ በሰፊው መሰረቱን የጣለው ኢፈርት (የወያኔ ንግድ ተቋም) በብቸኝነት የትግራይ ህዝብ ንብረት ነው ብሎ በይፋ መናገሩ፣ አሁንም መለስና የእርሱ ዘሮች የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በብቸኝነት በመጠነ ስፋት ከተቆጣጠሩት ለፖለቲካ ጥማታቸው ሊያደናቅፍ የሚችል ህብረተሰብ ሊኖር እንደማይችል የታሰበ መሰሪ አላማን ዘርቶ ስልጣንን ለመልቀቅ መለፍለፍ ከድጡ ወደ ማጡ የሚያመራ የቅዠት ጎዳና ነው፡፡

መለስ እነኚህንና መሰል ችግሮች ዘርቶ ስልጣኑን ለመልቀቅ ቢናገር ያውም በቦታው ላይ እንደፈለገው ሊጠመዝዘው የሚችለውን ግኡዝ የሆነ ሌላ የወያኔ አባል አስቀምጦ ዞር ማለቱ(መልቀቁ) ዶሮን ሲያታልሉዋት አይነት ጨዋታ ይሆናል።

በተጨማሪም ባለፈው እንዳየነው ሃገሪትዋ ካልዋት ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ውስጥ ከስድሳ አንዱ ሃምሳ ሰባቱ የትግራይ ተወላጆች እንደሆኑ አይተናል። በሌላው ጎን ደሞ የመለስ ዜናዊ አናሳ ቡድን በዋነኛነት ሃገሪቱ ያላትን ከፍተኛ ውሳኔ ሰጪ ቦታዎች ማለትም በሚኒስትር ደረጃ እንዴት እንደተቆጣጠሩት ማየት ተገቢ ይመስለኛል።

ከነዚህም ውስጥ በጥቂቱ፦

1. መለስ ዜናዊ ጠቅላይ ሚ/ር (ትግሬ)

2. ስዩም መስፍን የውጭ ጉዳይ ሚ/ር (ትግሬ)
3. በረከት ስሞኦን ማስታወቂያ ሚ/ር (ትግሬ)
4. አባይ ጸሃዬ የብሄራዊ ደህንነት አማካሪ (ትግሬ)
5. ሳሞራ ዩኑስ ጠቅላይ ኤታማጆር ሹም (ትግሬ)
6. ጌታቸው አሰፋ የደህንነት ሚ/ር (ትግሬ)
7. ስበሃት ነጋ የሰላምና የልማት አለማቀፍ ተቋም ዋና ዳይሬክተር እና በሚ/ር ደረጃ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ልዩ አማካሪ (ትግሬ)
8. አርከበ እቁባይ የስራ እና ከተማ ልማት ሚ/ር (ትግሬ)
9. ቴዎድሮስ አድሀኖም የጤና ሚ/ር (ትግሬ) ወዘተ...
10. አባ ጳውሎስ እና አባ ሳሙኤል የኦርቶዶክስ ቤ/ክ ሀላፊዎች

እነኝህ እንግዲህ ለምሳሌ ያህል ተጠቀሱ እንጂ በሌሎች በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ውስጥ ያለችሎታቸው በዘር ትግሬ ስለሆኑ ብቻ ተሰግስገው ህዝቡን ሲበዘብዙ የሚኖሩ ትግራዮችና፣ ከስንዴ መካከል እንክርዳድ እንደሚባለው ለሆዳቸው ያደሩ ስብእና እና ሞራል የጠፉባቸው የሌላ ብሔር ተወላጆችን ለመጥቀስ ይቻላል። ግን ጊዜን ማባከን ነው። እናም መለስ ይህንን ሁሉ የበሰበሰ ታሪክና በሽታ ትቶ ነው ስልጣን ለመልቀቅ የሚለፈልፈው።

ውድ አንባቢዎቼ ኢትዮጵያን ካለችበት ችግር ለማላቀቅ የጉልቻው መለዋጥ አይደለም መፍትሄው ወጡ እንዲጣፍጥ ባለሙያውም ቅመሙም ወሳኝነት አላቸውና የመለስ ስልጣን መልቀቅ ሳይሆን ጉዳዩ ወያኔ መለስ ወይም ህውሃት ከዚች ሰአት ጀምሮ አይደለም ኢትዮጵያን ለመምራት በኢትዮጵያ ውስጥም ለመኖር ዘመናቸው ያከተመ (expired) የሆነ ስለሆነ ይንን የተበላሻ አገዛዝና ዘረኛ መንግስት ፍጹም ገርስሰን እስካልጣልነው ድረስ ለውጥ ይመጣል ብሎ ማሰብ የቀን ቅዠት ይሆናል፡፡

እናም ላሳለፍነው የመከራ ዘመን እና ለታላቂቱ ኢትዮጵያ ብለን ከትላንቱ በበለጠ አንድ በመሆን መለስን ብቻ ሳይሆን ዘረኛውን የወያኔን ስርዓት ለመገርሰስ አንድ ሀገር! አንድ ሰንደቅአላማ! አንድ ህዝብ! እና አንድ አላማ! ብሎ መነሳቱ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው ፡፡

ህዝብ ሁሌም ያሸንፋል!!

ደቀ-መዝሙር